## በኢህአዴግና በኢዴአፓ-መድህን መካከል ለውይይት ከቀረቡት
## አጀንዳዎች ውስጥ ስምምነት የተደረሰባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ መድህን (ኢዴአፓ-መድህን) በተለያዩ መሠረታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ ለመወያየት የሚያስችላቸውን የጋራ አጀንዳ ለመቅረጽ ፤ ሁለቱም ፓርቲዎች የየራሳቸውን አጀንዳዎች አዘጋጅተው በቅድመ-ውይይት የንግግር ወቅት ካቀረቡ በኋላ ፤

አንደኛ ፤ በሰኔ ወር 1997 ዓ.ም እና በጥቅምትና በህዳር ወር 1998 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማና በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተውን ሁኔታ እንዲያጣራ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተቋቋመውን ኮሚቴ የሥራ ሂደት መከታተልን በተመለከተ በኢዴአፓ-መድህን በኩል የመወያያ አጀንዳ እንዲሆን የቀረበ ሲሆን ፤ በኢህአዴግ በኩል ይህ ኮሚቴ በፓርላማው የተቋቋመና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል በመሆኑ ፓርቲዎች የዚህን አካል እንቅስቃሴ የሚከታተሉበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ ይህንን ጉዳይ አጀንዳ አድርገን ልንወያትበት አይገባም የሚል ሃሳብ በመቅረቡ ፤

ሁለተኛ ፤ የታሰሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎችን በተመለከተ በኢዴአፓ-መድህን በኩል ውይይት እንዲደረግበት በአጀንዳነት ቢቀርብም ፣ በኢህአዴግ በኩል የነዚህ ግለሰቦች ጉዳይ በፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ የመወያያ አጀንዳ ሊሆን አይገባውም የሚል ሃሳብ በመቅረቡ ፣

በሁለቱ አጀንዳዎች ላይ ሁለቱም ፓርቲዎች ሊስማሙ ባለመቻላቸው ልዩነታቸው በቃለጉባኤ ተመዝግቦ ፤ በተስማሙባቸው አጀንዳዎች ማለትም

1. የህገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችና የህግ የበላይነትን በተመለከተ

2. የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአሰራርና የአባላት ስነ-ምግባር ደንብን በተመለከተ

3. የምርጫ ቦርድን በተመለከተ

4. መገናኛ ብዙሐንን በተመለከተ

5. የፖለቲካ ፓርቲዎችን የፋይናንስ ድጋፍን በተመለከተ

6. የውይይቱን ውጤት ማስፈፀሚያ ስልቶችና የክትትል አግባቦችን በተመለከተ በሚሉ ስድስት ዋና ዋና አጀንዳዎች ላይ ውይይታቸውን በገንቢ መንፈስ ለማካሄድ ተስማምተዋል።

ሁለቱ ፓርቲዎች ለመወያየት ከተስማሙባቸው አጀንዳዎች ውስጥ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችንና የህግ የበላይነትን በተመለከተ እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራርና የአባላት የሥነ ምግባር ደንብን በተመለከተ ተወያይተው ስምምነት ላይ ደርሰዋል።
በዚህ ስምምነት መሰረት ከዚህ የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥተዋል።

- የአገራችን ህገመንግስት ዓላማን በሰላማዊ መንገድ የማራመድና በነጻ የመደራጀት መብትን ለሁሉም ዜጎች ያጎናፀፈ መሆኑን እና በዲሞክራሲያዊ ስርአቱ ግንባታ ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ታግሎ ለማስተካከል ወይም ለመቀየር/ለመለወጥ የሚቻልበት አግባብ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠ መሆኑን በመቀበል ፣

- የአገራችን ህገ መንግስት የማይፈቅዳቸዉን የትግል ስልቶች ማለትም የሃይልና የዓመፅ አማራጮችን በመጠቀም የፖለቲካ አላማን ለማራመድ መሞከር ህገወጥ መሆኑን በመቀበል ፣

- ተቃዋሚ ፓርቲዎች በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ የሚያካሂዱት እንቅስቃሴ ለመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ መጎልበት የበኩሉን የማይተካ አስተዋፃኦ እንደሚያበረክትና ለዚህም በየደረጃው በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ አስፈላጊው ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርለት እንደሚገባ በመተማመን ፣

- ገዢው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመካከላቸው መቻቻልና ብሄራዊ መግባባት ተፈጥሮ ሁሉም ወገን የአገር ግንባታ ሃላፊነቱን መወጣት እንዲሚገባው በመተማመን ፣

- የመንግስት አካላት ዜጎችን በእኩልነትና በፍትሃዊ አኳኋን የማስተናገድ ህገ መንግስታዊ ግዴታና ሃላፊነት እንዳለባቸዉ በመስማማት ፣

- ፓርላማ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት መገለጫ እና አብላጫ መቀመጫ ያለው ፓርቲ ገዢ የሚሆንበትና አነስተኛ መቀመጫ ያለው ፓርቲ የሚያቀርበው ሃሳብ የሚደመጥበት ምክር ቤት መሆን እንደሚገባው በመተማመን ፣

- በፓርላማው ተቃዋሚ ፓርቲዎች አጀንዳ ከማስያዝ ጀምሮ በተሻለ ሁኔታ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል የሚሰጥ የአሰራር ደንብ ሊኖር እንደሚገባ በመተማመን ፣

- ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ችግሮችን በድርድር የመፍታት ባህል ያለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ በመገንዘብ ፣

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) እና የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ መድህን (ኢዴአፓ-መድህን) ከላይ የተጠቀሱትን መርሆዎች መሰረት በማድረግ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችንና የህግ የበላይነትን ማክበርን እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራርና የአባላት የስነ-ምግባር ደንብን በተመለከተ የሚከተለው ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

1. ሁለቱ ፓርቲዎች በህገ መንግስቱ አንዳንድ አንቀጾች ላይ ልዮነት ያላቸው መሆኑንና በልዮነቶቻቸው ላይ በህጋዊ መንገድ መታገላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በማክበርና በማስከበር የመንቀሳቀስ ግዴታ እንዳለባቸው ለመቀበል ተስማምተዋል።

2. ሁለቱ ፓርቲዎች ህገ መንግስቱ በህጋዊ መንገድ ስልጣን ለመያዝ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት ያለው መሆኑን በመገንዘብ ህገ መንግስቱ ከሚፈቅደው አግባብ ውጭ ስልጣን ለመያዝ በሚደረግ ጥረትና እቅድ ላለመሳተፍና ይህን የመሰለውን ህገ-ወጥ ተግባር ለመቃወም ተስማምተዋል።

3. ሁለቱም ፓርቲዎች ለሃገሪቱ ህገመንግስት ባለመገዛት የፖለቲካ አላማቸውን ከህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ውጭ በሀይል ለማስፈፀም ከተሰለፉ ድርጅቶችና ቡድኖች ጋር ድርጅታዊ ቁርኝት ላለመፍጠር እና በዚህ መልኩ የሚደረግ እንቅስቃሴ የህግ ተጠያቂነት በአገራችን እንዲነገለብት ጥረት ለማድረግ ተስማምተዋል።

4. የመንግስት አካላት በህገመንግስቱ ድንጋጌዎችና መንፈስ መሰረት ዜጎችን በእኩልነትና በፍትሃዊ አኳኋን የማስተናገድ ግዴታና ሃላፊነታቸውን በተግባር መወጣታቸውን ለማረጋገጥ ተስማምተዋል።

5. ሁለቱም ፓርቲዎች አባሎቻቸው ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎችንና የህግ የበላይነትን እንዲያከብሩና ማንኛውንም ህገ ወጥ ተግባር ከመፈፀም እንዲቆጠቡ የማስተማር ግዴታቸዉን ለመወጣት ፣ እንዲሁም የፓርቲዎቹ አባላት ህገ መንግስቱንና የህግ የበላይነትን ጥሰው በሚገኙበት ወቅት በአባሎቻቸው ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ተስማምተዋል።

6. ሁለቱም ፓርቲዎች በየአካባቢዉ በፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ተፈፅመዋል የተባሉ ችግሮችን በዝርዝር ለማቅረብና የጋራ ኮሚቴ አቋቁሞ ለመፍታት ተስማምተዋል።

7. በጥናት ላይ ተመስርቶ የተሻሻለውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራርና የአባላት የስነ-ምግባር ደንብ ተወያይተው መቀበላቸውን አረጋግጠዋል።

የኢህአዴግ እና የኢዴአፓ-መድህን ተወካዮች ከላይ የተዘረዘሩትን የስምምነት ነጥቦች በሙሉ ልብ ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ አቋም ይዘው በቀሪዎቹ አጀንዳዎች ማለትም ፣

1. የመገናኛ ብዙሃንን በተመለከተ ፣
2. የምርጫ ቦርድን በተመለከተ ፣

3. የፖለቲካ ፓርቲዎችን የፋይናንስ ድጋፍን በተመለከተ ፣

4. የስምምነቱ ማስፈፀሚያ ስልቶችና የክትትል አግባቦችን በተመለከተ ፣

በሚሉት ጉዳዮች ላይ በማተኮር ውይይታቸው እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ ይገልፃሉ።

ጥቅምት 7 ቀን 1999 ዓ.ም

| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር | የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ - መድህን |